«ቅኔ-ዘጌሾ!»

(ገሞራው ከገረ ስዊድን)

በስዊድንኛ ቋንቋ "G"ን ጂ ሳይሆን አነባበቡ «ጌ» ተብሎ ነው። በነሱ አነጋገር «ጌሾ» ማለት የነሰባቱ የዓለም ኃያላን (ሀብታም) መንግስታት የሚጠሩበት ምሕፃረ-ቃል ነው። በአማርኛ ቋንቋ ደግሞ በአልኮ መጠጦች ውስጥ አዕምሮን ቆንጠጥ እንዲያደርግ ተብሎ የሚጨመር የዕፅ ዓይነት ነው። በጠላው፣ በጠጁ፣ በአረቄው፣ በመሪሣው፣ በቦርዴው... ውስጥ ይገባል። በአስካሪነቱ የታወቀ ተክል ነው። ይችንቅኔ ስታነቡ ይቺን ነጥብ አስታውሱ።

______________________

ዛሬም የነገረ ዕፅዋትን መንገኒቅ እንደሳበኝ ነው። ቅኔ-ዘጌሾን ይዤ ቀርቤያለሁ። ከዚህ ቀደም ባቀረብኳቸው የነገደ-ተክሎች መቅድማዊ መግቢያ ላይ ያቀረብኩት መግለጫ ለዚህም ቅኔ ስለሚያገለግል መቅድማዊ መነሻነቱ የተጠበቀ ነው። የዛሬው ተክል ስም «ጌሾ» ይባላል። ጌሾን በጥሬ ስምነቱ ማንነቱን የማያውቅ ያገሬ ሰው ይኖራል ብዬ አላምንም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በሕይወቱ ሂደት ውስጥ በአንደኛው የዕድሜ ምዕራፍ ላይ ጣዕመ-ጌሾን በጠላው ወይም በጠጁ አለያም በአረቄው ውስጥ ሳይቀምሰው የቀረ አይመስለኝም። እንዴውም ከመቅመስ አልፎ አንድ የነሸጠው ዕለት በዛ አድርጎ ጨላልጦ ሳይሰክርም እንደማይቀር አምናለሁ። (ታሪኩን የመ. አ. ጠ. ማ. አባላት ይንገሯችሁ)

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ናዜራ ስሜት ባጋጠመው ጊዜ ጠጣ ጠጣ የሚል ሌጌዎን ያለበት ይመስል ጌሾ በባለሟልነት የሚሠየምበትን መጠጥ (ጠላ፣ ጠጅ፣ አረቄ...) ይቀምስና ዝብረር ብሎ ይውላል። በኔ ግላዊ ግምት ጌሾ ያለበት መጠጥ ሁሉ የሆነ አስካሪ መርዝ ያለው ይመስለኛል። ሀገር ቤት በነበርኩበት ዘመን ጌሾ ያለባቸውን መጠጦች በመቀምቀም ከአመት እስከአመት የሚሰክሩ ሰዎች እንደነበሩ አስታውሳለሁ። ከሰከሩ በሁዋላ የሚፈጽሙት ድርጊት ሁሉ ለኔ የኮሜዲ ድራማዎች ነበሩ። ጌሾ ውስጥ ያለው ምን ያህል መርዘኛ እንደነበር በድራማው አርቲስቶች አማካይነት ተረድቻለሁ።

ተክለ ጌሾ በአልኮላዊ መጠጦች ውስጥ ሁለ-ገብ ቅመም ሆኖ እንዲገባ ተመርጦ መቅረቡ አእመምሮን የሚቆነጥጥ ባህርይ ስላለው ነው። «መርዝም መዲኃኒት ሲሆን በጥበታ!» ብሎስ የለ? ባለቅኔው። ጌሾ የመርዝነት ባህርይ ያለው ተክል በመሆኑ አደገኞች ተብለው ከተመደቡ እጽዋት ጋር የቅርብ ዝምድና እንዳለለው ይነገራል። የዝምድና ሀረጋቸው በውል አይታወቅ እንጅ እንደነ ሀሺሽ፣ ማሪዋና፣ ኤልኤስዲ አክስቶቹ ሲሆኑ ይችላሉ። የቀሩትም መርዘኛ አስካሪ እጽዋት እነዕፀ-ፋርስ፣ እነአብሾ፣ እነዕፀኮምል አጎቶቹ ሲሆኑ እንደሚችሉ እገምታሁ። እነጫት፣ እነቡና፣ እነሲጋራ (ጥምባሆ) የቅርብ ዝምድና አይኑራቸው እንጅ የጌሾ ዝርያዎች ናቸው። እነዚህን ሁሉ መርዘኛ ነገደ-ዕፅዋት የሚገናኙበትና የሚዛመዱበት አንድ ሀረጋዊ ባህርይ አላቸው። ይኸውም የቀመሳቸውን ሁሉ «የሚያወፍፉ» መሆናቸው ነው።

እያንዳንዱ ሰው በነዚህ አስካሪያን ዕፅዋት ለመጠቀም የሚፈልግበትን ምክንያቶች የየራሱን መነሻ ሰበብ ይደረድራል። አንዳንዱ ሰው በኑሮ ላይ የሚፈጠርብኝን ጭንቀት ያስታግስልኛል ይላል። ሌላው ሰውደግሞ የደከመ የወሲብ ስሜቴን ያንቀሳቅስልኛል ይላል። የተቀረው ደግሞ የደነዘዘ አእምሮዬን ይስልልኛል ይላል። ዝርዝሩን መናገር ያሰለቻል እንጅ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚደረድረው የየራሱ ምክንያትአለው። ዛዲያንን የሁሉንም ምክንያት አሰባስበን ብንመረምረው የሚያመረቃ ማስረጃ ሊሆን አይችልም። ድሮስ ቢሆን «መርዝ» የሚያስጠጣ እንዴት ብሎ ጥሩ ምክንያታዊ ማስረጃ ሆኖ ያውቃል? እንግዲህ ይህን ሁሉ ሀተታ መዝናችሁ ባለ መርዝ የሆነውን ጌሾ በየበኩላችሁ እንድታጠኑት የበኩሌን አስተያየት እዚሁ ላይ እገታለሁ። ይህ ቅኔ በአዝማችነት የሚገለገልበት አንድ መንደርደሪያ ግጥም አለው።

ዕነሆ፦

«ሰው እያሰከረ - ገደል የሚከተው፣
ለምለም ቅጠል መስሎ - ስንቱን ያሰቃየው፣
ጌሾ አይደልም ወይ - በውስጡ መርዝ ያለው!»

_________________________________

## **ቅኔ ዘጌሾ!**

ዕልፍ አዕላፍ ዕፅዋት - በሀገሬ እንዳሉ፣
አስረድቻለሁኝ - ዘርዝሬ በሙሉ፣
ባለፈው ጥሁፌ - በየቅኔው ሁሉ።

በዛሬው ቅኔዬ - ተራውን የያዘው፣
«ጌሾ» የምንለው - አስካሪ ተክል ነው፣
እየከነተረ - ጠጭ ያስቸገረው፣
በየሄደበቱ - መረን የሚደፋው።

በመራራነቱ - ቆንጠጥ በማድረጉ፣
ጠላና ጠጅ ውስጥ - ይገኛል በወጉ፣
አስሚ ነው ተብሎ - ታውቆ ማስፈለጉ።

ለአረቄ ነክ መጠጥ - ነፍስነቱ ታውቋል፣
ህይወት እንደሚሰጥ - ህያው ሳልሆን አካል!

«ወይን ያስተፌስህ» ይላል - የድሮው መጽሃፍ፣
ጌሾን አስመልክቶ - ባለመርዙን ጅራፍ፣
ያን ልብ ሰላቢውን - በአሽሙር ሲደግፍ።

ጌሾ ያለበትን - የቀመሰ ሁሉ፣
ወፈፍ ያደርገዋል - ሁሉን እንዳመሉ።

አንዱን ያስለቅሳል - ሌላውን ያስቃል፣
አንዱን ልብስ አስጥሎ - እርቃኑን ያስሄዳል፣
የቀረውን ደግሞ - ሻምፓኝ ያስከፍታል፣
ድርጊቱ ብዙ ነው - ስንቱ ይነገራል?

እንደቅርብ አጎቱ - እንደዚያ እንደጫት፣
ዱካክ ያስይዝና - አርጎ አሻንጉሊት፣
ይጫወትበታል - በህልማዊ ቅዠት፣
ልቡን አመርቅኖ - ፈጥሮበት አዙሪት።

የማይሰራው የለም - ትንግርትና አባዜ፣
ከመጠኑ አልፎ - በተጠጣ ጊዜ።

ምን አያረገው አለ? - ተንኮለኛው ጌሾ፣
ከልቡ ውስጥ ገብቶ - እንደዚያ አብሾ።

ያሽከረክረዋል - በፈለገው መንገድ፣
የዋሁን ያገር ሰው - ቀልቡን ጥሎ እንዲያብድ!

መላ ቅጡን  አጥቶ - በወፈፌ ጠባይ፣
እንዲያብድ አድርጎታል - ቁምስቅሉን እንዲያይ!!

የጣለለትን ቁራሽ - ቁራጭ ቅንጣቢ፣
ውሻ አድርጎታል - ቆሼውን ሰብሳቢ።

የሚጥልለትን - አድርጎት ለቃሚ፣
ተጫውቷል ያ ጌሾ - ሆኖ እንደ «ሸሚ»።

የወደቀ ሸቀጥ - አርጎት ማራገፊያ፣
እንደሆነ አለ - የጥንብ መረፍረፊያ።

እንደዚያ ማድረጉ - ይፋ እየታወቀ፣
ጌሾ ነግሶ ኖሯል - ይፋ እየቦረቀ፣
ባለሙ ላይ ሁሉ - እያብረቀረቀ።

እንዳያስብ አርጎ - ደጉን ያገሬ ሰው፣
ባሪያ አድርጎታል - ጌሾ ባለጠላው፣
በሰከረ ቁጥር - ዘለዓለም ሊገዛው !

አያይጣል ነው አያድረስ - የዚያ ጌሾ ዕብሪት፣
ጨንቅላት ላይ ወጥቶ - ሲያጠፋ ህይወት።

ወገን አሳብዶ - መላ የሚያሳጣ፣
የታል እንደ ጌሾ - ቅንዝንዝ አይን አውጣ።

እንደተራ ሸቀጥ - ልዩ ቅራቅንቦ፣
ከየሀገሩ ላይ - ለቃቅሞ ሰብስቦ፣
መጣያ ያጣውን - ምናምን ከርካሳ፣
አጠራቅሞ አምጥቶ - ጭኖ በወሳንሳ፣
ጌሾ እያታለለ - ማራገፊያ አርጎታል፣
በመጠጡ አሳቦ - ይጫወትበታል፣
እንዳሻው አድርጎም - መረን ይነዳዋል።

እጅግ የሚገርመው - የጌሾ አሰራር፣
ሰጭ እየመሰለ - ይወስዳል በአኪር።

ያስደሰተ መስሎ - በመጠጥነቱ፣
በስተኋላ ያርዳል - በመርዛማነቱ።

ያስደሰተ መስሎ - ባልኮልነት ግልገል፣
ሰላቢ ነውና - ደህውን ይሰልባል።

በጌሾ ምክንያት - ስንቱን ወገን ከሰሯል፣
ያገኘ ሲመስለው - ስጋ ነፍሱን አጥቷል፣
እየቀመቀመ - መላ እርቃኑን ቀርቷል።

ጌሾ ባመጣው ጠነንቅ - ስንቱ ትዳር ፍርሷል፣
ቅመሱኝ እያለ - ስንት ሀገርስ ጠፍቷል!

ጌሾ እያዋዛ - በየሀገሩ ገብቶ፣
ስንቱን ቅኝ አርጎታል - በመጠጥ ጎትቶ?

ጌሾ እያዋዛ - ገብቶ ገጠር ገዳም፣
የስንቱን አጽም ነው - በትኖ እሚያስለቅም።

አጅሬ ያ ጌሾ - በጠጁ በጠላው፣ ባስለመደው አመል፣
ባሪያው ያደረገው - ስንቱ ይቆጠራል።

ሀገር ቤት ይቁጠረው - የተፈንጋዩን ሰው፣
ጌሾ እያባበለ - ዕመቅ የከተተው።

በሞራል በትምህርት - እንዲያም ሲል በእውቀት፣
ስንቱን አበላሽቷል - ጌሾ እሚሉት መቅሰፍት።

ህሊናን መርዞ - ባደገኛ  እጹ፣
ስንቱን አሳብዷል - ጌሾ በማመጹ።

ስሜት አረካለሁ - እያለ አታሎ፣
ጠጭውን ሰው ሁሉ - ረፍርፏል ገድሎ።

ጣእሜ ልዩ ነው - እያለ በመሰበክ፣
ስንቱን እየጋተ - አስኬደ በእንብርክክ!

እንዳጎቱ አብሾ - እንጎል እያጦዘ፣
አያ አጅሬ ጌሾ - ስንቱን አናወዘ?

ለሰው ልጅ መድህን ነኝ - ብሎ ቢፋሽክም፣
ለጥፋት ነው እንጅ - ለልማት አይሆንም፣
ስራው ሁሉ ሲታይ - በምናውቀው አለም።

ለምለም መሬት ሲያገኝ - ጌሾ መፈንደቁ፣
ሞቶ ተሟሙቶ - ከዚያም ላይ መውደቁ፣
ልምላሜ እንዲሰጠው - አውቆ ተማምኖ ነው፣
በያገሩ ዘልቆ - የሚንሰፈሰፈው።

ካልወቀጡት በቀር - ጌሾ ጠላ አይገባም፣
ጥሬውን ቢገባም - ከቶ አይስማም።

ስለዚህኮ ነው - መውቀጥ ያስፈለገው፣
ያለበለዚያማ - ከቶ አይጥምም ቃናው።

ልዩው ያገሬ ሰው - ትንታጉ አበሻ፣
ፈጥሮለታል ዘዴ - መሳይ ያን መዶሻ።

ከበስተግርጌው ላይ - ሙቀጫውን ተክሎ፣
ከላይ በስተራሱ - ዘነዘና አሎሎ፣
መሃል ላይ ይለዋል - ጌሾን አስተካክሎ።

ጌሾ ተቀጥቅጦ - እልኩ ካልገባ፣
ይሰብራል እንስራ - ምንተዳው ሰለባ፣
ይሉኝታ የለውም - ግንዱን የሚያባባ።

ለጋንም ለበርሜል - በጭራሽ አይራራ፣
ጥሬውን እንዳለ - ቢገባ ሳይፈራ፣
ሰባብሮ ይጥላል - በቆመበት ስፍራ።

በያገሩ ገብቶ - በሚሰራው ስራ፣
ሰው እያሰከረ - በሚፈጥረው ሴራ፣
ሕዝቦች አስቸግሯል - ያ ጌሾ መራራ!




ይህን በደል የሚያውቅ - የየሀገሩ ሰው፣
ጌሾን ነቅሎ ይጣል! - ከየግል ፈለማው።

ጌሾ እስካለ ድረስ - መስከርም አይቀርም፣
ከሰከሩ ደግሞ - መሳት አለ ምኔም፣
ራስን አዝቅጦ - ከምንም መላተም።

ተዝቆ አያልቅም - የጌሾ ስንክሳር፣
እንዲሁ ባጭሩ - ቢቀጬትም አያምር፣
ደግሞ ሌላ ጊዜ - ሳይበዛም ሳያጥር፣
መጻፍ ይሻላል - አጠራቅሞ ከበር።